# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ቛፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ !
አባዝተው ያሰራጩ !

ቁጥር 2 ግንቦት 14 2000 ዓ.ም


# የሱዳን ድንበር ሃገራዊ ክህደት ከፍተኛ ቁጣ እየቀሰቀሰ ነው

## "በትግራይ ያገኘነው በመተማ ከሰጠነው መሬት ይበልጣል"የወያኔ/ኢህአዴግ ባለስልጣናት

የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን አሳልፎ በመስጠቱ ከህዝቡና ከደጋፊዎቹ ሳይቀር ጠንካራ ተቃውሞና ትችት እየቀረበበት ነው።

ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የወያኔ/ኢህአዴግ አባላት እንደተናገሩት፣ በመካከለኛ አመራር ደረጃ የሚገኙ የህውሃት አባላት መሬት ለሱዳን መሰጠቱን አስመልክቶ በመገናኛ ብዙሃን የሚቀርቡት ዘገባዎች ታአማኒነት እንዲረጋገጥላቸው ለድርጅታቸው ጥያቄ አቅርበዋል። የህወሀት ባለስልጣናትም "በመተማ በኩል ለሱዳን ከሰጠነው 17 ቀበሌዎች የበለጠ በትግራይ ክልል በኩል ያገኘነው መሬት ይበልጣል።"የሚል መልስ በመስጠት ደጋፊዎቻቸውን ለማረጋጋት እየሞከሩ ነው።

የመለስ አገዛዝ በኤርትራ በኩል ያለውን የድንበር ውዝግብ ለመፍታት በተሳነው ማግስት በሱዳን በኩል ሌላ ውዝግብ የሚያስነሳ ድርጊት መፈጸሙ የተለያዩ አስተያቶች እንዲቀርቡ እያደረገ ነው። አንዳንድ ወገኖች "የህወሀት ባለስልጣናት በትግራይ ክልል ተጨማሪ መሬት አግኝተናል ማለታቸው አንድም አገር ወዳድ ከሆነው የትግራይ ህዝብ የሚደርስባቸውን ተቃውሞ ለማብረድ ሌላም የህወሀት ባለስልጣናት በስልጣን ላይ ለመቆት ያላቸው እድሜ አጭር መሆኑን ተገንዝበው ከአሁኑ መሸሸጊያ ይሆነናል ብለው የሚያስቡትን የትግራይን ክልል፣ የሌሎች ክልሎችን መሬት በመለወጥ ለማስፋት ማሰባቸውን ያሳያል" ይላሉ። ሌሎች ደግሞ በወያኔ የተበላሸ አመራር የመጣውን የኑሮ ውድነት እና ረሀብ ህዝቡ በቂ ትኩረት እንዳይሰጠው ለማድረግ ወያኔ የወሰደው እርምጃ ነው ይላሉ።

አንዳንድ ወገኖች ደግሞ "የትጥቅ ትግል ለማድረግ የሚያስቡ ሀይሎች በሱዳን በኩል መረማመጃ እንዳያገኙ ለማድረግ ወያኔ ለሱዳን የእጅ መንሻ ማቅረቡ ነው" ይላሉ።

በእነዚህ ወገኖች የሚያቀርቡት አስተያየቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በወያኔ ላይ የሚሰነዘረው ተቃውሞ እየበረታ መምጣቱን በየስፍራው የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን እየጠቆሙ። በአማራው ክልል ከኑሮ ውድነቱ በተጨማሪ የድንበሩ ጉዳይ የህዝቡ መነጋገሪያ ከሆነ መሰንበቱ ተገልጿል። በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ህዝቡ የህወሀት ንብረት የሆኑ መኪናዎችን አግቶ በመያዝ ህዝብ ተቃውሞውን እየገለጸ ነው።

## የመለስን ክህደት ምን ማድረግ ይሻላል?

ገጽ3 ዜና ሀተታ በሱዳን ድንበር ጉዳይ

## ስለ ግንቦት 7 መመስረት ወገን ምን ይላል?

### በርካታ መልእክቶች ደርሰውናል

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከተመሰረተበት ግንቦት 7፣2000 ዐም ጀምሮ የንቅናቄውን መመስረት የሚደግፉ በርካታ መልእክቶች እየደረሰው መሆኑን ንቅናቄው አስታወቀ።

ከአስተያየቶቹ በጥቂቱ በገጽ 2

## አጫጭር ዜናዎች

### የክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት

ወደ ጎረቤት ሃገር ሲኮበልሉ ተያዙ። በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሰሞኑን ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት የክልሉን ምክትል ፕሬዚዳንት ጨምሮ ሌሎች ሰዎች መታሰራቸው ተሰማ። በክልሉ የሚንቀሳቀሰው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ወተደራዊና የሲቪል

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

## ሚሊዮኖች በሞት አፋፍ ላይ ናቸው

### ህዝብ እርምጃ መውሰድ ጀምሯል

በሀገሪቱ የተፈጠረውን የፖለቲካ አለመረጋጋትና የኢኮኖሚ ድቀት ተከትሎ ኢትዮጵያውያን እህል ቀምሰው ህይወታቸውን ለማቆየት ከኑሮ ጋር ግብ ግብ ከገጠሙ ብዙ ቆይተዋል።

በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው ኢህአዴግ መራሹ መንግስት፤ለ አጠቃላይ የምግብና የሸቀጦች ዋጋ ንረት "ስግብግብ" ያላቸውን ነጋዴዎች በምክንያትነት ሲጠቅስ ከመቆየቱም በላይ ፤በዚህ ዙሪያ ቁጥጥር አድርጎ እርምጃ የሚወስድ ግብረ-ሀይል በፓርላማ ደረጃ ማዋቀሩ ይታወሳል፣ ፣ ሆኖም፣ ከወራት በፊት የተዋቀረው ይህ ግብረ-ሀይል ከሁለት መቶ በሚበልጡ የንግድ ድርጅቶች ላይ የማሸግ እርምጃ በወሰደበት በአሁኑ ጊዜ ፣ የኑሮ ውድነቱ እጅግ አስደንጋጭ ደረጃ ላይ ደርሱዋል።

በጎጃም፤በጎንደር፤በሲዳማና በሀረርጌ የሚገኙት ሪፖርተሮቻችን እንዳጠናቀሩት ዘገባ፣ የነጋዴዎችን እህል በማመላለስ የተሰማሩ አይሱዙ መኪናዎች ስራቸውን ካቆሙ ከሁለት ሳምንታት በላይ ተቆጥረዋል። በበርካታ የገጠር ከተሞች ህዝቡ፣ እህል የጫኑ መኪናዎችን ማገት ጀምሩዋል።

ወትሮ በለምነታቸው የሚታዎቁት የኦሮሚያና የደቡብ ክልሎች ሳይቀሩ በረሀቡ መጠቃታቸው የታወቀ ሲሆን፣ በመሀል አዲስ አበባም የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ 1000 ብር መግባቱን 'አዲስ አድማስ' ጋዜጣ ዘግቧል።

የጋዜጣው ዘጋቢ ያነጋገራቸው አረጋውያንም"በ 1966 እና በ 1977 ዓ. ም የተከሰተውን ድርቅ አይተነዋል፣ በዘመናችን {በ ዕድሜያችን } የዘንድሮውን ዓይነት ችግር አይተን አናውቅም' ብለዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የተ.መ.ድን መግለጫ ዋቢ በማድረግ ሲ.ኤን.ኤን ትናንት እንደዘገበው፤አዋቂዎችንና አረጋውያንን ሳይጨምር ከ ሰባት ሚሊየን በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ህፃናት በምግብ እጦት ለሞት ተጋልጠዋል።

ስልጣን በተቆናጠጡ ማግስት 'ራዕይዎ ምንድነው?" በሚል ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ "በቀጣዮቹ ጥቂት ዓመታት የኢትዮጵያ ህዝብ በቀን ሶስት ጊዜ ሲበላ ማየት ነው"ብለው የመለሱት አቶ መለስ፣ በሀያ ዓመት ቆይታቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀን አንድ ጊዜ እንከኳን የሚቀምሰውን ሲያጣ በማየታቸው ምን ይሰማቸው ይሆን ሲሉ ታዛቢዎች በምፀት ይጠይቃሉ። ተግባር ከቃላት በላይ ይናገራልና መልሱ ምንም እንደሚሆን እርግጠኞች ነን።

**አዘጋጆች**
ፋሲል የኔአለምና እና ደረጀ ሃ/ወልድ
የቀድሞ የአዲስ ዜና እና
የነጻነት ጋዜጣ አዘጋጆች

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

**የግንቦት ሰባት ድምጽ ጋዜጣ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ አቶ መሰፍን አማን፧አቶ ቸኮል ጌታሁን፧ሁሉም የቅንጅት ለአንድነትና ዴ ሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የነበሩ።

## ርዕሰ አንቀጽ

# ትግላችን፡ ብዙ ነገር ይጠይቃል

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ‘ የተሰኘው ድርጅታችን ዓላማና ፕሮግራሞቹን በግልፅ በማስቀመጥ በተለያዩ አቅጣጫዎች አበረታች እንቅስቃሴዎችን ጀምራል። ደግመን ደጋግመን እንደገለፅነው፤ዋነኛ ግባችን ሁሉም ዜጎች በእኩልነትና በነፃነት የሚኖሩባትን ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ዕውን ማድረግ ነው፤ ፤ይህን ለማድረግ ደግሞ አቅሙም፤አቁዋሙም አለን።

“በዲሞክራሲና በነፃነት” ስም በኢትዮጵያና በዜጎቹዋ ላይ የተጫነው የአገዛዝ ቀንበር በማያዳግም ሁኔታ መሰበር አለበት የሚል ፅኑ እምነት አለን።

አዎ!ኢትዮጵያ፤ለዕልፍ ልጆቹዋ ገህነም፤ለጥቂት ገዥዎች ገነት ከሆነች ዘመናት ተቆጥረዋል፤

ኢትዮጵያ፤ለብዙሀን ዜጎቹዋ ረመጥ፤ ለጥቂት ሹመኞች ጥገት ላም ከሆነች ጥቂት የማይባሉ ዓመታት አልፈዋል።

ስለ ዲሞክራሲና ስለ ህግ የበላይነት እየተደሰኮረ ባለበት በአሁኑ መንግስት ደግሞ፤ይህ ዓይነቱ የግፍ አገዛዝ እየተወጠረ፤እያበጠና እየተነፋ የሚፈነዳበት የመጨረሻው ጥግ ላይ ደረሰ እንጅ ከቶ ሊረግብ አልቻለም፤ ይህ አልሆነም ብሎ የሚከራከር ካለ፤ አቶ መለስ እንደሚሉት “መንገዱን ጨርቅ ያድርግለት”።

“በረሀ በሞቱት ባልንጀሮችዎ፤
ጫካ በወደቁት በጉዋደኞችዎ
ኢትዮጵያን ይማሩዋት ፈሪም አንልዎ”

ብለን እስክንጮኽ ድረስ፤ በምርጫ ካርዳችን የዘረርናቸው ደናቁርት ባለስልጣናት’ድምፃችን ይከበር!’ብለን ላነሳነው የመብት ጥያቄ የጥይት ምላሽ ሰጥተውናል። ለፍቅር ለእርቅና ለሰላም ጥያቄያችን፤ ራሳቸው የፃፉትን ጎደሎ ህግ ሳይቀር በግላጭ በመጣስ አስረውናል፤ ደብድበውናል፤ ገድለውናል። ”የደርግን ቀንበር ሰበርንላችሁ” ያሉን የትናንት ታጋዮች፤ ሁለት አስርት ሳይሞላቸው እነሆ ባንገታችን ላይ የብረት ዛንጂር አጥልቀዉ፤ የመብትና የነፃነት ጥያቄያችንን ከጥጋብ ቆጥረዉ’ ከ እንግዲህ የኢትዮጵያን ህዝብ ረግጦ መግዛት ነው’ የሚል አቋዋማቸውን በድፍረት አሳይተውናል።

እንግዲህ፤ንቅናቄያችን በግልፅ ያስቀመጠውን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ በዋነኛነት ትግሉን የሚያካሂደው ከነዚህ ጨካኞችና ጨቋዋኞች ጋር ነው፤ ፤

ስለዚህ፤ መላው የድርጅታችን አባላትና የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!ትግላችን፤በዘር ፖለቲካ በታወሩ ፤በውሸታቸውና በነፍሰ-ገዳይነታቸው በዓለማቀፍ ደረጃ በታወቁ ቡድኖችና -በሰላምና በዲሞክራሲ አርበኞች መካከል የሚካሄድ ነውና ጥንቃቄን ይጠይቃል።

ትግሉ፤ በጠመንጃ አገዛዝ በሚያምን የጥጋበኞች ስብስብና -የህግ የበላይነትን ለማስፈንበሚሹ ዜጎች መካከል የሚካሄድ ነውና ብልሀትን ይጠይቃል።

ትግሉ፤ወኔና ሞራላቸው በስኩዋር በተንበረከከ እንዲሁም ‘የራሴ’የሚሉት አቁዋም በሌላቸው ጥቂት የስልጣን ጥመኞችና - ሰማይ እንደ ናስ በተከነበለበት በብዙሀኑ የ ኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ስለሆነ ድፍረትን፡እልህንና ልዩ አገራዊ ፍቅርን ይጠይቃል።

ትግሉ፤ በጥቅም፣ በአምቻና በጋብቻ በተሳሰሩ፤ እንዲሁም መዋቅራዊ ግንዳቸውን እስከ ጎጥ ድረስ በዘረጉ ቡድኖችና -የዜጎችን እኩልነት ለማስፈን በተነሱ ሀይላት መካከል የሚካሄድ ስለሆነ ስክነትንና ማስተዋልን ይጠይቃል።

አዎ!ትግሉ፤አገራችንን መውጫ የሌለው መቀመቅ ውስጥ ለመጣል የመጨረሻው ጫፍ ላይ ከደረሱ ደናቁርት ፖለቲከኖች ጋር የሚካሄድ ስለሆነ ፍጥነትን ይጠይቃል።

አዎ! በሁሉም መስክ እጅግ የተወሳሰበውንና ጥልቅ ስር የሰደደውን ብልሹ ፖለቲካዊ አገዛዝ በእውነተኛ የዲሞክራሲ የነፃነትና የፍትህ ስርዓት ለመቀየር ስንነሳ በውስጥም በውጭም የተለያዩ ተግዳሮቶች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ፤ ትግላችን ከምንም በላይ ትዕግስትንና ብስለትን ይጠይቃል።

**ማንኛውንም መረጃ ከላይ በተቀመጠው የፖስታ አድራሻችን ይላኩልን የኢሜል አድራሻችን** pr@ginbot7.org **ነው።**

**ይችን ትንሽ ጋዜጣ በሚችሉት መንገድ ሁሉ እያባዙ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ልሳን ያድርጓት።**

ከገጽ 1 የዞረ **የክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት**

ተቐማት ላይ በሰነዘረው ጥቃት ብዙ ጉዳት ማድረሱ ሲታወቅ፣ይህን ተከትሎ የክልሉ ባለስልጣናት ህዝቡን በብቃት አላደራጃችሁም፣ እንዲሁም ከሽፍቶች ጋር ተባብራችሁአል በሚል ምክንያት ከስራና ከሃላፊነት እንዲነሱ መደረጉ ታውቓል።በዚህም መሰረት የክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ ሳቢል ባኪት ወደ ሱዳን በመሻገር ላይ እንዳሉ ተይዘው አሁን በፌደራሉ የደህንነት ሃይላት ቁጥጥር ስር መሆናቸው ሲታወቅ፣የአሶሳ ከተማ ከንቲባ የነበሩት አቶ ከሊፋ መሃመድ ባሁኑ ሰአት ወደ ጎረቤት ሀገር እንደገቡ ለማወቅ ተችሎአል።

ከዚህ በተጨማሪም አብደልባሲት አህመድ፣ ሉቅማን ሳልህ፣አወድ ሀሺን፣ ሙስጠፋ ሙሳ፣ ዛርቅ ሃምዳን እና ሌሎች የክልሉ ባለስልጣናትና ግለሰቦች በእስር ላይ እንደሚገኙ ለደህንነት መስሪያ ቤት ቅርበት ያላቸው ምንጮቻችን ገለጹ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ በመላ ሃገሪቱ ይህ አይነቱ የታጣቂዎች እንቅስቃሴ እየጎላ መምጣቱንና በስልጣን ላይ ያለው መንግስትም በሁሉም አቅጣጫዎች መወጠሩን ያሳያል ብለዋል።

**ለመከላከያ ሰራዊት አባለት በሙሉ**

***መለሰን በቃን በሉት። የሀገር ክህደት ሴራ ተባባሪ አንሆንም በሉት። ከአንተ ጋር በታሪክና በህዝብ ተጠያቂ አንሆንም በሉት። ለወገን ለሃገር ቁሙ!***

ከገጽ 1 የዞረ **ወገን ምን ይላል**

አመጽና ሰላም የማይሰማሙ ነገሮች ቢመስሉም ዘንባባውን በአንድ እጅ ይዞ በሌላው እጅ መብትን ለማስከበር ቡጢ መጨበጡ ተገቢ ነው። "ወያኔን በማይገባው ቋንቋ እናናግረዋለን። የማይገባው የፍቅር ቋንቋ ነው" ተባለ። የሚገርመው በማይገባው ቋንቋ አነጋግሮ እንዴት ያደምጠናል ተብሎ እንደተሳበ ነው። እንዴትስ መልእክት ሰው በማይገባው ቋንቋ ማስተላለፍ ይቻላል። ኢህአዴግ የፍቅር ቋንቋ የማይገባው በመሆኑ ወደ ግድያና ወደ እስራት ሄደ። ምን ያስገርማል። በኢህአዴግ መዝገበ ቃላት የፍቅር ትርጉሙ ፍራቻ ነው። መማጠን ደግሞ ንጣፍ ሁነህ ልራመደብህ የሚል መልእክት የሚያሰተላልፍ ነው። በማይገባው ቋንቋ በማናገር ኢህአዴግን የሚይዘውን የሚጨብጠውን ያጣ እብድ አድርገነዋል። ይህ ከነበረ ግባችን ተሳክቶልናል። የምንፈልገው ግን እርቅን ሰላምን ድርድርን እንዲቀበል ከሆነ በሚገባው ቋንቋ ማናገር ይገባናል። ወያኔ ጣት እቆረጣለሁ ብሎ በእብሪት ሲደነፋ በሰለጠነ መንገድ ከብልግናው እንዲመለስ መምከር ብቻ ሳይሆን፣ የእሱንም ጣት መቁረጥ እንደሚቻል ሊነገረውም፣ አስፈላጊ ከሆነም ቆርጦ ማሳየትም ያስፈልጋል። ለከት የሌላቸው አምባገነኖች በሙሉ የሚገባቸው ቋንቋ ይህ ነው። ከእዛ በተረፈ የሰላም ዘንባባውን ከእጃችን እስካልጣልነው ድረስ ሁኔታው ሲመቻች እርቅን ድርድርን

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

ከገጽ 2 የዞረ. ወገን ምን ይላል

ለመቀበል፣ ለቡጢ የተቋጠሩ ጣቶቻችንን ዘርግተን በፍቅር ባላንጣቻችንን ለመዳሰስ የተሻለ እድል ይኖረናል። የሰላም ራእይ የሌለው አመጽ አይኑረን። ተገደን ወደ አመጽ ተገፍተናል። አመጽ የማይቀር ከሆነ በሚገባ ለታሰበበት በቅልጥፍና በተደራጀ በማያወላውል እምነት የሚመራ አመጽ ማካሄድ ይኖርብናል። እንደገና ተሰባሰበን ለክብራችን ለነጻነታችን ለመብታችን እንነሳ። እናንተ ካመረራችሁ እኛማ ከመረረን ከረመ።

እንየው ከመሃል አራዳ አዲስ አበባ

እርግጥ ነው ብዙ ተብሎ ብዙ ተነግሮ በተግባር ግን የታየው ባዶ ነው። ይህ አልሆነም ተብሎ በራሳችንም በወገናችንም ላይ ተስፋ ቆርጠን፣ ባርነትና ድህነትን ተቀብለን፣ በስንት መስዋእትንና ጀግንነት ቀድምቶቻችን ያተረፉልን ሃገር፣ ጸረ-ኢትዮጵያ ስልጠናና የጀርባ ታሪክ ባላቸው አካላት ሲበተንና ሲዋረድ ዝም ብለን እንቀመጣለን ወይ? ወይንስ እየወደቅንም እየተነሳንም፣ ከአንድ ውድቀት ወደ ባሰ ውድቀት እየተገላበጥንም፣ አንድ ቀን የነጻነት የፍትህ የብልጽግና ምኞታችን መሳካቱ አይቀርም ብለን ትግላችንን እንቀጥላለን? እኔ ምርጫ የለንም ባይ ነኝ። በግሌ ቃል ኪዳናችሁን አክብራችሁ በተግባር እስከተጋችሁ ድረስ ቀና ህልማችሁን ህልሜ አድርጌ ከጎናችሁ ለመቆም፣ የሚከፈለውን መስዋእተንት ለመክፍል ዝግጁ ነኝ። የጥርጣሬና የምጸት ሰላባ ሆኘ፣ "እባክህ ሁሉም ከንቱ ነው" እያልኩ ባርነትን በጸጋ የሚቀበል ህሊና ፈጥሬ መኖር አልችልም። የትዳር ባልደረባየም በእዚህ ትስማማለች። እንዴት ነው የምናገኛችሁ፣ እንዴት ነው የምንረዳችሁ።

ተከስተ ከፍራንክፈርት ጀርመን

ነጻነት እንደገጸ በረከት የታደለበት ሃገር የለም። ዛሬ ሰልጥነዋል የምንላቸው ሀገሮች ውስጥ የምናየው ዴሞክራሲና ፍትህ የከፍተኛ መስዋእትነት ውጤት ነው። በተለይ በኢትዮጵያ የተንሰራፋው የአፈና አይነት በሰፈነባቸው ሀገሮች በአቋራጭ መብትና ነጻነት ተገኝቶ አያውቅም። ህሊና የሌላቸው አረመኔዎች ህሊና ይገዙ ይሆናል ግዜ እንስጣቸው፣ ጠንክሮ በመናገርና አናስከፋቸው የሚሉ አባባሎች አምባገነኖች ምን እንደሆኑ አለማወቅ ነው። አለማወቅ ካልሆነ ደግሞ ትረጉም በሌለው የፖለቲካ ተሳታፊነት ስም እራስን እየሸነገሉ ለመኖር የሚደረግ ግብዝነት ነው። ይህን ተረድቶ ማስተካከያውን ማድረግ ተገቢ ነው። ቆሽቱ የበገነው መላው የሃገሪቱ ህዝብ የሚፈልገው ይህንኑ ነው።

መስተዋት ከደቡብ አፍሪቃ

ከገጽ 1 የቀጠለ ዜና ሀተታ

## የመለስን ክህደት ምን ማድረግ ይሻላል?

«ያዲያቆነ ሰይጣን ሳያቁስ አይለቅም» ይላሉ እመው ። ሃገራችንን ኢትዮጵያን ባህር በር አልባ በማድረግ የጀመረው የመለስ ቅድመ ሥልጣን ክህደት ፤ ዛሬ ደግሞ «መሬት ለዘይት ልዋጭ!» እያለ በኢትዮጵያ ምእራባዊ ድንበር የክህደት ንግዱን ቀጥሏል። ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጉዳዩን ይፋ ሲያደርጉ የመለስ የመጀመሪያ ምላሽ ፍፁም ዝምታ ነበር። የሱዳን መንግስትና ጋዜጦች ግን የዕውነትነቱን ፍንጭ ሲያሰሙ ዝምታ እንደሚጎዳው ስለተረዳ «ገና ውጥን ነው እንጂ፤ በወረቀት ላይ የፈረምኩትን ገና በመሬት ላይ ችካል ሳልቸክል፣ ክህደቱን ሳላጠናቀቅ የምትናገሩ ሁሉ ወራዳ ናችሁ» ብሎ በውጪ ጉዳይ ሚኒስተሩ ስም መግለጫ አወጣ ። በመጀመሪያ ለምን ዝምታን መረጠ? ኋላስ ስድብን ምን አመጣው?

የታላቁ ቴዎድሮስ የትውልድ ቀበሌዎች ለክህደት መቅረባቸው በመንግስቱ የራሱ መግለጫ እንኳዋ አከራከሪ አልሆነም ። ይህ የክህደት መንስኤ ጥንቱኑ ከሻእቢያ ጋር ውጥ ረት ውስጥ ላለመግባትና ቀለብ ሰፋሪዎቹን ምእራባውያንን ለማስደሰት ሲል በሕገ መንግስቱ ላይ ያሰፈረው አንቀፅ ሁለት፤ የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና የድንበር አንድነት ጉዳይ ለድርድር የሚያቀርብ እምነት የጨበጠ መሆኑን ነው ። ወያኔ/ኢህአዴግ፣ኢትዮጵያን ፣መስዋእትነት ከፍላ ነፃነቷን አስከብራ እንደኖረች የብዙ ሸህ ዘመናት ባለታሪክ ሃገር አድርጎ ከማየት ይልቅ ፤ በዘመነ ቅኝ አገዛዝ ከመቶ አመት በፊት የተመሠረተች አድርጎ ስለሚያይ፤ ዳር ድንበሩዋንም ለድርድር የሚቀርብ አድርጎ ለማየት ተገደደ ። ኢትዮጵያ ከቅኝ ገዢዎች ጋር ተገዳ የገባቻ ቸውን የድንበር ውሎችም እንደ ወሳኝ በመውሰድ ሃገሩን ማስደፈር የአለም አቀፍ ህግን አክባሪነት አድርጎ ሜዳሊያውን በደረቱ ላይ አንጠለጠለ ። ይህ ከእመ ኢትዮጵያ ጥላቻ ፤ ከታሪክ ዕውቀት ድህነት ፤ ከተራ ዱርዬ ጥጋብ የመነጨ ሥልጣን፤ በምንወዳት ሃገራችን ኢትዮጵያ ላይ ነብስ ዘርቶ እንዲጎማለል በመፍቀዳችን ልናፍር፤ ልናዝን ፤ ልንንገበገብ ይገባናል ። መለስ ለኢትዮጵያ የሚመጥን መሪ ከቶ አይደለም ። ይህንንም የምንለው በግንቦት 97 ስለተሸነፈ ብቻ አይደለም ። የሃገር ክህደቱ ጥልቀት ፤ ሃገር ወዳድ ከሆነው ኢትዮጵያዊ ቆሌ ጋር የሚሄድም ስላልሆነ ነው ። ይህ በህዝብ ድምፅ የተረታ አውሬ፤ በፀጥታና መከላከያ ሃይሎች ድጋፍና ምርኩዝ ብቻ የቆመ ነው።

መለስ በምርጫ ያሸነፉትን የቅንጅት መሪዎች አለም በቃኝ ከወረወረ በሁዋላ፤ የተነሳበትን የህዝብ ተቃውሞና የምእራባውያን መንግስታት ኩርፊያ ለማረሳሳት በማሰብ ፤ በ«ሃገር ልትወረር ነው» የሃሰት ጩኸት «አልከይዳን በሱማሊያ እደመስሳለሁ» ብሎ ገና ድክድክ በሚል የህዝብ ተስፋ ላይ ወረራ አካሄደ ። ቀላል ይሆንልኛል ብሎ የገባበት ማጥም የመከላከያ ሃይሉን መመታት ፤ መዋ ረድና ሬሳ መጎተት አስከተለ ። ሠላማዊ የስልጣን ሽግግር እንዳይኖር ለመከላከል በሃገር ላይ የፈፀመውን ክህደት ለመሸፈን የወሰደው የሱማሌ ወረራ ዛሬ መቀበሪያው መከላከል የነበረበት የኢትዮጵያ የመከላከያ ሃይል ፤ በወራሪነት ሲሰማራ ፤ መለስ ከበስተጀርባው ከሱዳን ጋር በመተባበር በምእራብ ድንበሩ በኩል በኢትዮጵያ ላይ ወ ረራና ክህደት እየፈፀመ ነው ።

የኢትዮጵያ የመከላከያ ሃይል ተልእኮ መሆን የነበረበት ሃገርን ከወረራ መከላከል እንጂ ፤ በ15 አመታት የርስ በርስ ጦርነት የደከሙትን ጎረቤቶቹን መውረር አልነበ ረም ። የህዝብ ድምፅ እንዳይሰረቅ የተሰለፉ ሰላማዊ ዜጎችን በጥይት መረሸን አልነበ ረም ። ለአሽማቂዎች ውሀና የግመል ወተት ያቀረቡ የኦጋዴን ኢትዮጵያውያን እናቶችን ክብረ ንፅህና መግሰስና እንደ ዱር አውሬ ማባ ረር አልነበረም ። ለዚህም ነበር ቅንጅት «መቼም አሁን ለመሸነፍ ዝግጁ ስላልሆንክ የአምስት አመት ተጨማሪ እድሜ ልንሰጥህ ፈቃደኛ ነን። ያንን ከማድረጋችንና ፓርላማ ከመግባታችን በፊት ግን የፀጥታና የመከላከያ ሃይሎች እንዲሁም ሚዲያው ከገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ነፃ መሆን ላይ መስማማት አለብን» ብሎ ባለ ስምንት ነጥብ ቅድመ ሁኔታዎችን ያቀረበው ። መከላከያ ሀይሉን ይህን ከመሰለ ውርደት ለመከላከልና ከተልዕኮው ለሚያዘናጉት የሥልጣን ጥመኞች መሳሪያ ከመሆን ይልቅ፤ ሃገር የመከላከልና ድንበር የመጠበቅ ተልእኮው ላይ እንዲያተኩር ነበር ፤ ከገዢው ፓርቲ ነፃ ሆኖ እንዲተዳደር በመለስ እግር ሥር ወድቀን የለመንነው ። የፈራነውም አልቀረ ፤ ይሄው ደረሰ ። የአሉላን ስም ሲሰሙ ይብረከረኩ የነበሩ ማህዲስቶች እንኩዋ የትግራይና ጎንደር ጀግና የተሰየፈበትን ለም ሃገር በእዝ ከሚቀበሉበት ደረጃ ሊደርሱ ችለዋል ። ዕድሜ ለመለስ ክህደት ።

ወያኔ/ኢህአዴግ ቅርብ የሆኑ ሰዎች፤ «እንዴት እንዲህ አይነት ስህተት ትሰራላችሁ? ፤ እኛ ደጋፊዎቻችሁንስ ለምን ታስቀቁናላችሁ?» ሲሉዋቸው ፤ የነመለስ መልስ «በመተማ በኩል ለሱዳን ከሰጠናቸው 17 ቀበሌዎች የበለጠ መሬት ፤ እኛ በትግራይ በኩል አግኝተናል ፤ አጅሁም» የሚል መሆኑን በተደጋጋሚ ሰምተናል ። የመጨረሻ መደበቂያችን የሚሉትን «የትግራይ ብሄርተኝነት» በተራ ብልጣ ብልጥነት አታልለው ፤ ደጋፊያቸው በኢትዮጵያዊነቱ የተሰማውን ቁጣ ለማብረድና ብሎም መጠቀሚያቸው ለማድረግ ያውጠነጠኑት ተራ ውሸት እንደሆነ ጥርጣሬስ እንኩዋ የለንም። እንኩዋን አዲስ መሬት ለትግራይ ሊያሰጥ ባድመንና ኢሮብን ለኤርትራ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን ግን የትግራይ ህዝብ እንዳስቸገረው በተደጋጋሚ ለፈረንጆች የሚገልፀው መለስ መሆኑን የትግራይ ህዝብ ከማንም በላይ ያውቀዋል።

የዚህ ሥርአት መለያ ባህርያት ፤ ውሸት ፤ ማጭበርበርና ፤ ተራ የእረኛ ጥጋብ መሆኑን ፤ ዛሬ እንኩዋንስ ሠርቶ አደሩ ህዝብ ፤ የሥርአቱ ተጠቃሚዎች ራሳቸው ሊክዱ ከማይችሉበት ደረጃ ላይ መድረሳቸውና ፤

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ከገጽ 3 የዞረ የመለስን ክህደት

ካፈርኩ አይመልሰኝ በሚል ፈሊጥ « በምዕራቡም አለም ፖለቲከኞች የሚያደርጉት ተመሳሳይ ነው ፤ ኢህአዴግ ምን የተለየ አደረገ?» እስከማለት መድረሳቸው የሚጠቁመን ነገር ቢኖር የዚህ ሥርአት ዕድሜ እያጠረ መምጣቱን ፤ ውድቀቱም በጣም ቅርብ መሆኑን ነው :: በተጠቃሚዎቹ ጥርጣሬ ውስጥ የገባ ስርአት ከርሞ ይሰነብታል ማለት ከንቱ ነው :: ህዝብ ከልጆቹ ጉሮሮ እየነጠቀ ለነገ ብሎ በባንክ ያስቀመጠውን ተቀማጭ ገንዘብ በዋጋ ግሽበት ቀምቶ ለፖለቲከ ሸሪኮቹ በኪሳራ እያበደረ (በኦፌሴል የዋጋ ግሽበትና የማበደሪያ ወለድ ሂሳብ መሰረት እውነተኛው የመበደሪያ ወለድ ከዜሮ በታች 20 በመቶ አካባቢ ነው) የከመራቸው የመስተዋት ፎቆች የሚያንፀባርቁት ነገር ቢኖር ፤ ልክ እንደ ደርጉ የመለስ የስብሃትና የበረከት መንግስት ሃገሪቷን አራቁቶ ወደ ግብአተ መሬቱ እየተሸቀዳደመ መሆኑን ነው :: «መንገዱን ጨርቅ ያድርግለት» ከማለት በስተቀር ከቶ ምን ይባላል?

መለስን እንዲህ ዐይን ያወጣ ክህደት ለመፈፀም ምን ገፋፋው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው :: በአለም አቀፍ ደረጃ የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ዴሞክራቶችን ወደ ዋይት ሃውስ የሚያመጣ ከሆነ፤ ኢትዮጵያውያን በኦባማ የምረጡኝ ዘመቻ ላይ ከሚያደርጉት መጠነ-ሰፊ ተሳትፎ አንፃርና ኦባማ ራሱም በአፍሪካ አምባገነን መንግስታት ላይ ሊከተል ስለሚችለው ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብትን ከእርዳታ ጋር የማቆላለፍ ፖሊሲ ስለፈራና ይህም ቻይና በሱዳን ላይ ከመሠረተችው የበላይነት ጋር ተዳምሮ ፤ ኢትዮጵያንም በዚሁ የቻይና ካምፕ ለመደመርና ከምእራቡ ሲያኮርፍ የሚሄድበትን መንደር አዘጋጅቶ ለመቆየት ሊሆን ይችላል :: በተጨማሪም እነ ጄኔራል አል በሺር በቻይና አማካይነት ያደረጉት ተፅእኖ ሊኖር ይችላል :: በሁለተኛ ደረጃ የነዳጅ ዘይት ዋጋ እየናረ መጥቶአል :: ከቅርብ አመታት ወዲህ ሱዳን የነዳጅ ዘይት አቅራቢ ሆናለች :: ኢትዮጵያም ዘይት ከሱዳን ማስገባት ጀምራለች:: ይህንንም ሥራ ለማቀላጠፍ ከሱዳን ወደ ሽሬ እንዳሥላሴ የሚዘረጋ የባቡር ሃዲድ ውጥን አለ :: መለስ ከተማሪነት እድሜው የሚያስታውሰው ነገር ቢኖር በ1966 አም የነበረው እዚህ ግባ የማይባል የነዳጅ ዘይት ዋጋ ጭማሪ ከፖርቱጋል እስከ ኢትዮጵያ ለብዙ መንግስታት መገልበጥ ምክንያት መሆኑን ነው :: ያ አደጋ አሁንም መኖሩን መለስ ይረዳል :: ሱዳን ለኢትዮጵያ የነዳጅ ዘይት ዋጋ ቅናሽ ለማድረግ ተስማምታ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል :: መለስ በተቃዋሚው ላይ የሚያደርገው እመቃ መመረርንና ወደ በረሃ መውረድን ሊያስከትል እንደሚችል ከራሱም ተሞክሮ ያውቀዋል :: ከግንቦት 97 ወዲህ ደግሞ በህዝብ መብት ላይ የሚያደርገው ለከት ያጣ ግፍ የትጥቅ ትግሎችን እንደሚያበረታታ ገብቶታል :: የመብት እመቃውን በመሸሽም ሆነ ለሥራ ፍለጋ ወደ ሱዳን የገቡት ኢትዮጵያውያን ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ያውቃል :: በትጥቅ ዝግጅት ላይ ያሉም ሆኑ የተሰማሩ ሃይሎች ይህን ረጅም የሱዳን ድንበር እንደሚጠቀሙበት ይገምታል ፤ መረጃውም ሊኖረው ይችላል :: ባንፃሩም የኤርትራን መንግስት ለመገልበጥ ያለው ዝግጅት የተጠናቀቀ መሆኑንና 13 ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሰባስበው አንድ ግንባር መመሥረታቸውን የነመለስ መንግስት አውጆአል :: ኤርትራ ከሱዳን ጋር የመሠረተችውን መልካም ግንኙነት ለመናድም ሆነ ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የተደራጁት የኤርትራ ግንባሮች በሰሜናዊና ምእራባዊ ኤርትራ የትጥቅ ስምሪት ለማድረግ እንዲችሉ የሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር ትብበር አስፈላጊ ነው :: ስለ ሥልጣን ከማሰላሰል እረፍት የማያውቀው የነመለስ ድኩማን አእምሮ ፤ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ግቦች ሁሉ ለመጨበጥ የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ ለሱዳን በመስጠት የአል በሺርን ወዳጅነት ማግኘት ይቻላል ብሎ አሰላስሎአል :: የመለስ አይነት ትዕቢተኛ መንግስት ያልገባው ነገር ግን ተዋናዩ እርሱ ብቻ አለመሆኑን ነው ::

የነመለስ መንግስት ግብአተ መሬት ተቃርቦአል ስንል ግን ፤ ያለትግል ይወድቃል ፤ ሃገርና ወገን ሳይጎዳ ገሸሽ ይላል ማለታችን አይደለም :: በደነበረ ቁጥር አገር ምድሩን እንደሚያስስ ፤ አረጋውያንና ባልቴቶችን ሳይቀር እንደሚገድል ፤ በ10 ሺህዎች እንደሚያስር ፤ ከግንቦት 97 ድላችንና ፤ ዛሬ እስር ቤቱን ሞልተው ከሚገኙት በ10 ሺህ የሚቆጠሩ ኦሮሞዎች ፍዳ የተማርነው ነው :: ግን ምን ምርጫ አለን? ልመናና ምልጃ የወያኔ/ኢህአዴግን ልብ የሚያራሩ ሳይሆኑ ፤ ጥጋቡ ሞልቶ እንዲፈስ የሚጋብዙት ብቻ መሆናቸውን ለ17 አመታት ተንበርክከን የለመንንበት ጉልበት አሻራና ፤ በአሻራችንም ልክ እየናረ የመጣው የነመለስ ጥጋብና ቅጥ ያጣ የሃገር ክህደት የሚመሰክሩት ነው :: «የውረድ እንውረድ መንገዱን አልፈለጉትም፤ ሠላም ጠምቶአቸዋል» ብሎ ፤ ከዚያ ጋር የሚመጣጠን መለሳለስ ፤ ከአንገት መድፋታችን ጋር የሚመጣጠን ሩህሩህነት ፤ ከትብብራችን ጋር የሚመጣጠን ሃገር ወዳድነት ከነስብሃት መንደር አልታየም :: «ሃገር ተወረረ» ብለን የትግራይ እናቶቻችንን ለመከላከል ስንዘምት : ተሯሩጦ አልጀርስ ሄዶ መፈራረም ፤ በምርጫ አሸንፈነውም «ግዴለም አምስት አመት ግዛ» ስንለው : በአንፃሩ ያሸነፈውን ፓርቲ መሪዎች ዘብጥያ መወርወር ፤ የፓርቲዎችን ስምና አርማ እንደፈለገ ሲቀማ ፤ «ግዴለም በሌላ ስም እንደገና ሀ ብለን እንደራጃለን» ቢሉም : «ከፈለግሁ አልፈቅድላችሁም - እስቲ ምን ትሆናላችሁ» ሲል ነው የተደመጠው :: በዚህ ሁሉ ተግባሩም ግልፅ ያደረገው ነገር ቢኖር : ለልመና አፋችንን በከፈትን ቁጥር ሊሸናብን የወጠረው መሆኑን ብቻ ነው :: የዚህ ባለጌ ሥርአት ምርኩዝ ሆነው የሚያገለግሉት የፀጥታና የመከላከያ ሃይሎች እንዲህ አይነቱን ዋልጌ ፤ በእናት አባቶቻቸው : በእህት ወንድሞቻቸው፣ በአክስት አጎቶቻቸው ጫንቃ ላይ ሲጎልቱበት አይገባም :: በቃህ! ሊሉት ይገባል :: በሃገር ከሃዲ ላይ አፈሙዛቸውን ሊያዞሩበት ተገቢ እንጂ ነው:: ለህዝባችን ደግነትና ትሁትነት አትመጥንም! ወጊድ! ማለት ይጠበቅባቸዋል:: ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ነው ነገሩ :: ከሚወድቅ ባለጌ ሥርአት ጋር ተዳብሎ በየቤተክርስቲያኑ ደጃፍ ለማኝ ከመሆን ፤ የመከላከያ ጦሩ : «እኔ የአንድ ፓርቲ መሳሪያ አይደለሁም : የህገመንግስቱ ዘብ ነኝ : ከህዝብ ጀርባ ሃገር እየቆረሰ የሚያድል ከሃዲ የምሸከምበት ጫንቃና አብሬም የምወድቅበት ምክንያት የለም» ብሎ አምርሮ ሊነሳ ይገባዋል :: ከህዝብ አብራክ ከወጣ የህዝብ ጦርም የሚጠበቀው እንዲህ ዐይነት ወገንተኝነት ነው :: ለህዝብ የቆመ ወገንተኝነት :: ራስን ከውርደት የሚያድንና ፤ ሠራዊቱ እስካሁን የከፈለውን መስዋእትነት የሚያከብርና የሃገር ሞገስነቱን የሚያጠናክር ወገንተኝነት ::

በዚህ ትግል ሁሉም ዜጋ የራሱ ድርሻ አለው:: መለዮ ለባሽ ባየ ቁጥር ሊስትሮውም ጫማውን እየጠረገ ብሶቱን ሊነግረው ፤ በውይይት ታክሲ ላይም ሲሳፈር «እንወዳችሁዋለን ግን ለባለጌ አገዛዝ መሳሪያ አትሁኑ» ብሎ በመማጠን ፤ ውሃ ሊለምኑ ወደ ግቢ መጥተው በር ሲያንኳዋኩ «እኔን ይጥማኝ ብሎ ውሃውን ሰጥቶ: ከመሄዳቸው በፊት ግን «አገዛዙን ለመለወጥ አቅሙና መሳሪያው ያለው በእጃችሁ ነው» ብሎ በማስታወስ ፤ ቀጣይ የሆነ የሥነ አእምሮ ጦርነት በማከሄድ ሥርአቱን ከቆመበት ምርኩዝ መነጠል ይቻላል :: **በተጨማሪም ግንቦት 20 ቀን የነመለስን የ17 አመታት የግፍ አገዛዝ በመቃወም ሁሉም ባለበት ቦታ ልክ ከጠዋቱ 2 ሰአት ሁሉም ዜጋ በልቡ 17 ጊዜ «በሀገሬ የምታደን አውሬ፤ ክብር የሌለኝ ፍጡር ሳልሆን ፤ በፈጣሪ አምሳል የተፈጠርኩ ሰብአዊ መብት ያለኝ ሰው ነኝ»** እያለ ባለበት ቀጥ ብሎ በመቆም ለአገዛዙ ያለውን ተቃውሞ ሊገልፅ ይችላል :: እንዲህ ኢምንት የሚመስሉ እርምጃዎች በወሰድን ቁጥር : የአንድነት ሃይላችን እየበረታ ፤ የመለስና የአሽቃባጮቹ መንግስት ቅስም እየተሰበረ : ጥጋቡ እየከሰመ : ብሎም እየተገራ ፤ ውሎ አድሮ አንድም ሁሉን የፖለቲከ ሃይሎችን ያከተተ ጉባኤ እንዲጠራና ራሱም እንዲሳተፍ በዚህም መንገድ ወደ ተረጋጋና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በጋራ እንድንጉዋዝ፤ አለያም በተባበረ ትግል እንዲወድቅ ማስገደድ እንችላለን :: ሁላችንም ራሳችንን ለነመለስ እብሪት ሳናጋልጥ በአቅማችን ማድረግ የምንችለውን ካደረግን የዚህ ቅስማችንን ለመስበርና የታሪካዊ ጠላቶቻችን ሎሌ ሊያደርገን የተነሳን ባለጌ ስርአት እንዳልነበር ማድረግ ይቻለናል :: አይዞን ኅበዝ !!

---

### ለመከላከያ ሰራዊት አባላት በሙሉ

***መለሰን በቃን በሉት። የሀገር ክህደት ሴራ ተባባሪ አንሆንም በሉት። ከአንተ ጋር በታሪክና በህዝብ ተጠያቂ አንሆንም በሉት። ለወገን ለሃገር ቁሙ!***

---

**የዴሞክራሲ ሥርአት በሀገራችን መገንባቱ አይቀሬ ነው!!!**